*የመጽሐፍ ግምገማ*

**ግንቦት 7፣ ኢትዮጵያ፡ እኮ ምን? እንዴት?**
***ደራሲ፡ ክፍሉ ታደሰ***
**(ሰኔ 1998 ዓ ም) ዋሽንግተን ዲሲ፣ ኬ ኤንድ ኤስ ፕሬስ፤ 256 ገጽ**

***ገምጋሚ፡ ዶ/ር ጌታቸው መታፈሪያ***

**በ1997 ዓ ም በኢትዮጵያ የተካሄደው ታሪካዊ የሆነው አገራዊና ክልላዊ የምርጫ ሂደትና ውጤት ከአእምሮአችን ጨርሶ ሳይጠፋ ይህንን ወቅታዊ ጽሁፍ ለአንባቢ ማቅረባቸው ታላቅ አስተዋጽኦ ነው፡፡ መጽሐፉ የምርጫውን ሁኔታ፣ የፖለቲካ ተዋንያንና እንዲሁም በምርጫው ጊዜና ከዚያም በኋላ በተከሰተው ሁኔታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሠለባ የሆኑትን ሰዎች ዕጣ እድል በሥዕላዊ አገላለጽ አቅርበውታል፡፡ ደራሲው ሁኔታዎችን የመዘገቡት በሥፍራው በመገኘት፣ ለሁኔታው ቅርበት ያላቸውንና አድራጊ ፈጣሪ የሆኑትን ሰዎች በማነጋገር፣ የመንግሥትና የውጪ አገር ዘገባዎችን፣ አሰተያየቶችና ጽሑፎች ላይ በመመርኮዝ ነው፡፡ እነኚህን የምርምር ሁኔታዎች ያጠናቀረ ጽሑፍ ክብደት የሚሠጠው ነው፡፡ ደራሲው ያዩትንና የሠሙትን ከመመዝገብ አልፈውም ከሁኔታዎች በመነሳት አስተያየቶችንና ምክርም ለግሰዋል፡፡ ስለዚህ፣ ይህ መጽሐፍ ስለ 1997 ዓ ም ምርጫ ከሚሠነዘረው ገለጻ ባሻገር ትምህርት ሰጪና በተለይም በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ የተሠማሩት ሁሉ ግንዛቤ የሚያገኙበትና ለሚወስዱት የፖለቲካ እርምጃ ቆም ብለው እንዲያስቡበት የሚያደርጋቸው ይመስለኛል፡፡**

ደራሲው ሁኔታዎችን በበለጠ ለማስረዳት የራሳቸውን ገጠመኞች ቢነግሩንም፣ እንደ አንድ ገለልተኛ ፀሃፊ ያቀረቡት ጽሑፍ ይመስላል፡፡

መጽሐፉ 12 ምዕራፎች ከዋቢዎች ጭምር አካቷል፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ፣ በኢትዮጵያ የምርጫ ፖለቲካ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት (የፖለቲካ ፓርቲዎች ባልነበሩበት ሁኔታ) መጀመሩንና በደርግ ዘመን ደግሞ ምርጫው በአንድ ፓርቲ (የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ) አባላት መሐከል ብቻ የሚካሄድ እንደነበር ያሳያል፡፡ የእነኘ ـህ የሁለቱ መንግሥታት የምርጫ ፖለቲካ ዓላማ ዴሞክራሲንና የህዝብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ ሳይሆን የገዢውን አካል ህጋዊነት ለማረጋገጥና ተቀባይነትን ለማግኘት ነበር፡፡ በኢህአዴግ ዘመን አምስት አገራዊና ክልላዊ ምርጫዎች በ14 ዓመታት ውስጥ የተካሄዱ ሲሆን፣ ካለፉት ሁለት ሥርዓቶች (መንግሥታት) ምርጫዎች ለየት ባለ መልኩ በኢህአዴግ ዘመን በብሔርና በቋንቋ ላይ የተመሠረተ ምርጫ ሲሆኑ የተካሄዱት፣ ሂደቱ የተከናወነውም ከአንድ ብሄረሰብ በተውጣጣ ጠባብ ቡድን እዝ ስር ነው፡፡ የሚካሄዱት ምርጫዎችም አገራዊ (ኢትዮጵያዊ) ሳይሆኑ ክልላዊ (የብሄረሰባዊ) ስብዕና እንዲኖራቸው ከመደረጉም በላይ፣ ጠንካራ የመንግሥት ተቀዋሚ ኃይሎች ባሉባቸው አካባቢዎች አስከፊ ሁኔታዎች ተከስቶ የንጹሐን ደም ፈሷል፡፡ ሹማምንቶቹም ሆኑ ተመራጮቹ ህልውናቸው የሚጠበቀውና ጥቅማቸው የሚከበረው ለዚህ አናሳ የገዥ ክፍል በሚሰጡት አገልግሎትና ታማኝነት ነው፡፡ እትብታቸው ከገዥው ክፍል ጋር የተቆራኘ ስለሆነ ያ ቁርኝት ከተበጠሰ ህይወት አይኖራቸውም፡፡ ስለዚህ፣ ዴሞክራሲ፣ ግልጽነት፣ ብቃትና (merit) ለመራጩ ህዝብ ተጠያቂነት የዚህ መንግሥት ዓይነተኛ ምግባሩ አይደሉም፡፡

ወደ 1997 ዓ ም ምርጫ ዝግጅት ስንመጣ መጽሐፉ እንደሚነግረን ኢህአዴግ ከሁለት ዓመት በፊት ቀደም ብሎ ዝግጅት እንደጀመረ ነው:: ቅስቀሳው፣ ገንዘቡ፣ ተመራጮች፣ ወዘተ፣ ተዘጋጅተውና ኢህአዴግ አዎንታዊ ገጽታውን ለህዝቡ ሲያስረዳ ቆይቶ ነበር:: የተማሪው ቁጥር መብዛት፣ የትምህርት ተቋማት መበራከት፣ የአውሮፕላንና የጤና ጣቢያዎች መስፋፋት፣ የመልካም አስተዳደር መመስረት፣ የዴሞክራሲ መስፋፋት፣ በአጠቃላይ ኢህአዴግ ለእድገትና ለእኩልነት ያደረገው አስተዋጽኦ በስታቲስቲክስ በተደገፈ መልክ በብዙሃን መገናኛ ይቀርብ ነበር::

በተቃዋሚው ጎራ የነበረው ሁኔታ ግን የተለየ ነበር:: ግማሾቹ ገና እራሳቸውን ያሰባስቡ ነበር:: ኋላም "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" የሚል መፈክር መቀረጹንና ካልተባበራችሁ አንረዳም የሚል ግፊት እንደነበር የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት በአሜሪካ ሲመሰረት ተገልጽዋል፡፡ ይህንን በተመለከተም ጠ/ሚኒስቴር መለሰ ዜናዊ ሲተቹ፣ "44 የኢህአዴግ ጠላት ነን የሚል ሰውና ድርጅት ከሚኖር አንድ ላይ ሰብሰብ ብሎ ቢቀርብ ትግሉ ለኢህአዴግ ይቀልለታል" በማለት ለአንድ ጋዜጣ አስተያየት መስጠታቸው ይታወሳል:: (ገጽ 25)

ይህ ሁኔታ በዚህ እንዳለ ራዕይ 2020 የተባለው ፕሮግራም ኢትዮጵያ ከ25 ዓመታት በኋላ ምን እንደምትመስል የሚያገናዝብ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በበርካታ ምሁራን ተሳታፊነት መካሔዱና የአገሪቷን ችግሮችና መፍትሔዎች መዘርዘራቸው ለኢትዮጵያውያን አንድ ዓይነት ግንዛቤ አስጨብጦ የነበረ ሲሆን፣ የሕዝቡ ስነልቦና ከፍ እንዲልና እይታውም እየጠራ እንዲሄድ መርዳቱ ተጠቅሷል፡፡ የኢህአዴግን የሸር አሠራር ህዝቡ ቀደም ብሎ ቢያውቅም፣ ተቃዋሚዎቹ ካላሸነፉ ኢትዮጵያ የከፋ ሁኔታ ሊገጥማት እንደሚችል በሚገባ ተረዳ::

በሁለተኛው ምዕራፍ እንደምናየው፣ መንግሥት ምርጫውን በአሸናፊነት እንዲወጣ ሁኔታዎች ሁሉ አስቀድመው ተመቻችተው ነበር:: እንደሚታወቀው፣ የብዙሃን መገናኛዎች፣ ምርጫ ቦርዱ፣ የመንግሥት መዋቅሮች፣ ወዘተ፣ ለዴሞክራሲና ለህዝብ የቆሙ ሳይሆኑ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ናቸው:: ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ኅብረት ቀደም ብሎ ያስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ተቀባይነት አላገኙም ነበር:: ለምሳሌ፣ ኅብረት እንደጠየቀው የምርጫ ቦርዱ ቢበወዝ ኖሮ የምርጫው ውጤት ልዩ መልክ ሊይዝ ይችል ነበር:: ያንን ግን ኢህአዴግ በምንም መልኩ ሊቀይር እንደማይችል አቋም ወሰደ::

ይህ እንዲህ ሆኖ እያለ በተቃዋሚው ጎራ ውስጥ መከፋፈል ተፈጠረ:: ከኅብረት ውስጥ የመኢአድና የኢዴፓ መውጣት የኢህአዴግን ልብ ሞቅ ሲያደርግ፣ በብዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ግን ቀዝቃዛ ውሃ ቸልሶበታል:: ከኅብረት የወጡት ሁለቱ ድርጅቶች መዋሃድ ሲጀምሩ፣ "የመኢአድ ዓላማ በውህደት ስም ኢዴፓን ማክሰም ነው" በሚል ክስ ሂደቱ ብዙም አልተጓዘም:: (ገጽ 42)

ምርጫ 1997 ዓ ም ሊደረግ ጥቂት ወራት ሲቀረው ቀስተ ደመና የሚባለው ድርጅት ተፈጥሮ ለቅንጅት መመሥረት አስተዋጽኦ ከማበርከቱም በላይ፣ በመኢአድና በኢዴፓ መሐል የአስታራቂ ሚና ተጫውቷል:: ስለ ቀስተ ደመና ታሪክ መጽሐፉ በምዕራፍ 3 ላይ በጥሩ ሁኔታ አስቀምጧል:: የዚህ ድርጅት መፈጠር የኢትዮጵያን የፖለቲካ መልክዓ ምድር በአጭር ጊዜ ውስጥ በስፋትና በጥልቀት ለውጧል ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ያም ሆኖ ግን፣ እንደማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳለው መታወቅ አለበት:: ብዙ ምሁራንን ማሰባሰቡ ጠንካራ ጎኑ ቢሆንም፣ እንደ መጽሐፉ ገለጻ አብዛኛዎቹ በፖለቲካ ትግልና በድርጅታዊ አሰራር ልምድ

አልነበራቸውም። አገርንና ወገንን ከከፋ ሁኔታ እናድን ብለው ራሳቸውን ለመስዋዕትነት ማቅረባቸው ከግል ጥቅም በላይ መቆማቸውና አሁን ደግሞ ሰብዓዊ መብታቸው ተደፍሮ የፖለቲካ እስረኞች ሆነው እስር ቤት መንገላታታቸው ከጠንካራ ጎናቸው መሀል ሊጠቀስ የሚችል ነው። ይህንን ስል የድርጅቱ አባላት በቀጣይነት የሰከነ አመራር ለመስጠትና የላቀ የፖለቲካ ሥራ ለመሥራት እራሳቸውንና ድርጅታቸውን ከመገምገም ይቆጠቡ ማለት አይደለም። በተለይም የፖለቲካ መሪዎቻቸው በእስር እያሉ ከኢህአዴግ ሰለባ ያመለጡት የድርጅቱ መሪዎች ከመደበኛው የፓርቲ ፖለቲካና የቢሮክራሲ አሠራር ለወጥ ያለ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

ምዕራፍ 4 ስለ ምርጫው ውድድር አጀማመር ሲሆን የሚያትተው፣ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው የሆነውንና የሕዝቡን ትኩረት የሳበውን በፓርቲዎች መሐከል የተደረገውን የፖለቲካ ክርክር ይዘረዝራል። ይህ ክርክር ሶስት ውጤቶችን አስመዝግቧል ማለት ይቻላል። 1/ የህዝቡን ግንዛቤ ከፍ ከማድረጉም በላይ ዴሞክራሲ ምን እንደሆነ ሊያስገነዝብ ችሏል። በተለይ ወጣቱ ወደ ፖለቲካ ፊቱን እንዲያዞር ረድቷል፣ 2/ በክርክር መድረኩ የቀረቡት የኢህአዴግ (የመንግሥት) ተወካዮች ያቀረቧቸው ነጥቦችንም ሆነ አሃዞች ሕዝቡ ጆሮ ዳባ ልበስ ያላቸው ሲሆኑ፣ ሕዝቡ ከአገዛዙ የተረፈው ነገር የሌለውና በዚህ መንግሥት ስር ኑሮ እንዳልተሻሻለለትና የበይ ተመልካች መሆኑን፣ 3/ ተቃዋሚ ድርጅቶች የኢህአዴግን ደካማ ጎኖች እየጠቀሙ እነሱ ግን ለአገሪቷ የተሻለ አጀንዳና ራዕይ እንዳላቸውና የሥራ መስክ እንደሚከፍቱ፣ ችጋርና ረሃብን እንደሚቀርፉ፣ ወዘተ ተናገሩ። ይህ በዚህ እንዳለ፣ ምርጫውን ቢያሸንፉ ቃላቸውን መጠበቅ አለመጠበቃቸውን መተንበይ ባይቻልም፣ አነጋገሮቻቸው ተስፋ ሰጪዎች ነበሩ።

የክርክር ሂደቱ ዴሞክራሲያዊ ቢሆንም፣ ለአምባገነኑ መንግሥት ግን ማን ምን አለ በማለት አንዳንድ መሪዎች የጥቃት ዒለማው ሆኑ:: ኢህአዴግ አስቀድሞ እነኚህ ተቃዋሚ ኃይሎች መንግሥትን በኃይል ለመገልበጥ፣ ህገ መንግሥቱን ለመናድ (የዶ/ር ነገደ ጎበዜን መጽሐፍ በዋቢነት በማቅረብ) እንዲሁም እንደሩዋንዳው ኢንተርሃምዌይ አንዱን ዘር ለማጥፋት የተዘጋጁ ናቸው ብሎ ወነጀላቸው:: ታሪክ እንደሚያሳየን ግን፣ በሩዋንዳው ዘር ማጥፋት የተሰማራው በመንግሥት የሰለጠነ ልዩ ኃይል ነበር:: ኢህአዴግ ይህንን ቃል የተጠቀመው እራሱ የጠነሰሰው ነገር ሰለነበር ህዝቡን ቀደም ብሎ ለማዘጋጀት ኖሯል:: የዓግአዚ ልዩ ጦር በሕዝቡ ላይ የዘመተው፣ መንግሥት "የዘር ማጥፋት" የሚለውን ሃሳብ አስቀድሞ ለመከላከል በሚል ሰበብ በማቅረብ፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች፣ ደጋፊዎች ወይም ተጠርጣሪዎች፣ በተለይም በወጣቱ ላይ ለመዝመት በቅድሚያ የወሰደው ደባ ነበር:: ከምርጫው በኋላ የተከሰተው ሁኔታ ሲታይ፣ በመንግሥትና በሕዝቡ መሐከል የነበረው ልዩነት እየሠፋ ሄደ:: ኢህአዴግ በፍቅር ሳይሆን በማስፈራራት፣ አገር የሚያስተዳድር ሳይሆን አገር ረግጦ የሚገዛ ፀረ-ሕዝብ መሆኑን አስመሰከረ:: በዴሞክራሲ ሂደትና በሠላም ለውጥ ሊያመጣ የተሠለፈው ወጣት ላይ አደገኛ ቦዘኔ በማለት ኢህአዴግ ዘመተበት:: በስራ መስክ መጥበብ ምክንያት ወጣቱ ለደረሰበት ችግር ተጠያቂው ኢህአዴግ መሆኑ ግን አያጠያይቅም::

በሌላ መልኩ በጣም አሳሳቢ ነው የምለው፣ ሥልጣን ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶቹ እጅ ቢገባ ኖሮ ለዚህ ታላቅ አገራዊ ሃላፊነት ምን ያህል ተዘጋጅተናል ብለው ሃሳብ እንደገባቸው መሪዎቹ ለደራሲው መግለጻቸው ነው:: በእርግጥ ይህ አሳሳቢ ጉዳይ ቢሆንም፣ ደርግም ሆነ ኢህአዴግ ለዚህ ታላቅ አገራዊ ኃላፊነት እንዳልተዘገጁ የታወቀ ነው:: አገሪቷ ለገባችበት ችግር አስተዋጽኦ

ያደረገው አንደኛው ጉዳይ ቀደም ብሎ መሪዎችን ለከፍተኛ ኃላፊነት አለመኮትኮት፣ አለመዘጋጀትና ተመክሮ አለማካበት ነው። ጥሩ የውጊያ ገድል ያስመዘገበ ግለሰብ የወጣለት አስተዳዳሪ፣ ወይም ኀበዝ አስተማሪና መልካም መሪ ላይሆን ይችላል። ቁም ነገሩ ግን፣ ልምድ ያላቸውን ማሰባሰብ፣ ለመማር መዘጋጀትና ከመናገር በፊት መስማትን መምረጥ ነው። መሪዎችን መኮትኮትና ማዘገጀትን በተመለከተ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ከወዲሁ ሊያስቡበት ይገባል እላለሁ።

ተቃዋሚ ድርጅቶች ኢህአዴግን በሚገባ የመረመሩት፣ የፈተሹትና ያጠኑት አይመስልም። በመጽሐፉ ላይ እንደተጠቀሰው፣ በልበ ሙሉነት ኢህአዴግን እናሸንፋለን ሲሉ፣ ኢህአዴግ የሞት ሽረት ትግል ሊያደርግ እንደሚችል፣ እነሱ ደግሞ ለኢህአዴግ ጥቃት ምን መልስና መከላከያ/መከታ ሊያደርጉ እንደሚገባቸው መላ ምት አቅርበው፣ አውጥተውና አውርደው የተወያዩበትና ስትራተጂ ያዘጋጁበት ሁኔታ አልነበረም። ደራሲው በመጨረሻው ምዕራፍ እንደገለጹት፣ የህወሃትን ታሪክ ብናስተውል ገና ጫካ እያለ ሠላም ፈጠርን እያለ ለእርቅ ድርድር የመጡትን በተዘዋዋሪና በቀጥታም ቢሆን እንደሚያጠፋ፣ በአንድ እራስ ሁለት ምላስ እንዳለውና ፀባዩ አሁንም እንዳልለቀቀው ነው። ይህንን ከግምት ውስጥ ማስገባቱ ይጠቅም ነበር።

ከግንቦት 7 ታሪካዊ ምርጫ በፊት የተደረገውን ታላቅ ትዕይንተ ሕዝብ በመመዝገብ፣ የነበረውን የሕዝብ ስሜት ለዴሞክራሲያዊና ለሠላማዊ ለውጥ የነበረውን ጉጉት መጽሐፉ ካስቀመጠ በኋላ፣ በምዕራፍ 5 ውስጥ የምርጫውን ቀን ሁኔታ በዘገባ መልክ አቅርቧል። የሕዝቡን ሰላማዊነት፣ ጨዋነትና በምርጫው ላይ የጣለውን ተስፋ ያሳያል። የምርጫው ዕለትን፣ "በሚሊዮኖች የሚቆጠር የኢትዮጵያ ሕዝብ የሠርግ

ታዳሚ ሆኖ የዋለበት ቀን ነበር" ብለውታል ደራሲው። (ገጽ 85-86)

ያ የዴሞክራሲ ብርሃን ከመቅጽበት ጨለመ። ጠ/ሚኒስቴሩ ሥልጣናቸውን የተነጠቁ ስለመሰላቸው ማስጠንቀቂያ አዋጅ አወጁ። በገዢው ክፍል ውስጥ ክፍፍል ታየ፣ ዕድሜ ለኢህአዴግ የሚሉትም ከኢህአዴግ በኋላ ጥቅማቸው የሚቀር መሠላቸው፣ ባጠቃላይ ስርዓቱ ያፈራቸው ክፍሎች በኢህአዴግ መሸነፍ ተደናገጡ። ጥቅማቸውን ለማስከበርም ከሕዝቡ ሳይሆን ከኢህአዴግ ጎን ተሰለፉ። ኢህአዴግ ይሸነፋል ብለው ስላላሰቡ የማምለጫ ብልሃት አላዘጋጁም ነበርና!

መንግስትም ተቃዋሚዎችም በየበኩላቸው አሸነፍን አሉ። ሁለቱም፣ የሕዝብ ድምጽ ተሰረቀ በማለት ምርጫው እንዲጣራላቸው ጠየቁ። እዚህ ላይ መጠቀስ የሚያስፈልገው ሁኔታ አለ። ቅንጅት ባብዛኛው አሸናፊ ቢሆንም፣ ሕዝቡ የቅንጅትን ማኒፌስቶ አንብቦ፣ ድርጅቱም በሕዝቡ ውስጥ ገብቶ የሠራውና ያጎለበተው ድርጅታዊ ሥራዎችና የመሣሰሉት ኖረው ሳይሆን ይህ ምርጫ የቅዋሜ ምርጫ (protest vote) ነው በሚሉትና ሌላ አስተያየት ባላቸው መሀል የሃሣብ ልዩነት እንዳለ እዚህ ላይ ማስታወሱ አስፈላጊ ነው። ደራሲው እንደገለጹት፣ በወቅቱ ተቃዋሚቹ ለሕዝብ የሚደርስ የራሳቸው ጋዜጣ እንኳን አላዘጋጁም።

ከምርጫው በኋላ የተከሰተው ኢሰብዓዊ ሁኔታ ኢህአዴግን ከደርግ ጋር አነጻጽሮታል። ለምሣሌ፣ እንደደርግ የቀይ ሽብር ጊዜ የሟች ቤተሰቦች አስከሬን ለመቀበል "በአመዛኙ መቶ ብር ከፍለዋል"። እንዲሁም፣ አንዳንዶቹ 300 ብር የከፈሉበት ደረሰኝ ይዘዋል። (ገጽ 118) ከዚህ በተጨማሪ፣ የዝዋይ፣ የጨሪሳ፣ የሁርሶ፣ የብር ሸለቆ፣ የደዴሳ ታሣሪዎች የደረሰባቸው ግፍ ከደርግ አልፎ ከወራሪ ጦርና

ከአፓርታይድ ደቡብ አፍሪቃ ሁኔታ ጋር የሚያመሳስል ነው::

ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው በምዕራፍ 9 እንደተገለጸው የህወሃት ስውር መንግስት (the invisible state) ነው:: ስለህወሃት የስውር መንግስት የተጻፈ ባይኖርም፣ ደራሲው ከዚህ ድምዳሜ የደረሱት ቡድኑ ከሚያካሂዳቸው ድርጊቶችና ከራሱ ከህወሃት ታሪክ በመነሳት ነው፣ "ኢትዮጵያ ሁለት መንግስት ነው ያላት:: አንደኛው ኢትዮጵያውያንም ሆነ ዓለም የሚያውቀው በጠ/ሚኒስቴር መለሰ ዜናዊ የሚመራው፣ ከሚኒስቴሮች ጀምሮ እስከ ቢሮ ዳይሬክተሮች የሚዘልቅ መዋቅር ያለው መንግሥት ነው::" (ገጽ 154) ሁለተኛው፣ ስውር መንግስቱ ሲሆን፣ ከጠ/ሚኒስቴር ጀምሮ እስከ ቀበሌ፣ እስር ቤቶች፣ የገበሬ ማኅበራት፣ ዝቅተኛ የወታደር እርከን ድረስ የተዘረጋ ነው:: ይህ የስውር መንግስት ህግ አውጪውን፣ የስራ አስፈፃሚውንና የፍትህ አካሎችን በስውር ይቆጣጠራል:: በውጪ ኤምባሲዎች ውስጥ የዋና ፀሃፊነቱን ቦታ የሚይዙት የስውር መንግሥቱ ቀጥተኛ ተጠሪዎች ሲሆኑ አምባሳደሮቹ ለስሙ ነው ቦታውን የሚይዙት:: ይህ የስውር መንግሥት የአገሪቱን ካዝና፣ የጦር ኃይል፣ ወዘተ፣ የሚቆጣጠር የፈረጠመ አናሳ ቡድን ነው ማለት ነው:: ደራሲው የአገሪቱን አመራር ሁኔታ ለማስረዳት የሰምና ወርቅ ግንኙነት ምሳሌን ተጠቅመዋል:: ሠሙ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚባለው ሲሆን፣ ወርቁ በህወሃት የሚመራው ስውር መንግሥት ነው:: በሌላው አገር የጓዳ ካቢኔ (kitchen cabinet) እንደሚባለው የአማካሪዎች ቡድን ሲሆን፣ የኢትዮጵያው ግን ከዚያ የበለጠ አድራጊና ፈጣሪ ሲሆን፣ ተግባሩም የብዙሃኑን ሳይሆን የጥቂት ሰዎችን ጥቅም ለማስከበር የቆመ ነው:: ስለዚህ፣ መልካም አስተዳደር፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት የሚባሉ አሰራሮች በኢትዮጵያ ሁኔታ እርባና የለሽ ናቸው እንደመጽሐፉ አገላለጥ:: ይህን ሁኔታ በተመለከተ ከዚህ በፊት አንዳንድ

ምሁራን ሃሳቡን ያነሱ ቢሆንም፣ ጠለቅ ባለና የመንግሥቱን ባህርይ በሚያሳይ መልኩ ሲቀርብ ግን ይህ የመጀመሪያው ሳይሆን አይቀርም።

በመጽሐፉ እንደተጠቀሰው፣ ይህ ስውር መንግሥት ሁለት ተቃራኒ የሆኑ አጀንዳዎች አሉት። ይኸውም፣ "በግራ እጁ ዴሞክራሲን ይዟል፣ በቀኙ ደግሞ የትግራይ ብሔረተኝነትን ተሸክሟል።" (ገጽ 157) ይህ ሁኔታ በእኔ አስተያየት ሠፋ ያላ ጥናት እንዲደረግበት የሚጋብዝ ነው። ዴሞክራሲ ለዚህ የስውር መንግሥት ፀሩ ነው። ስለዚህ፣ ዴሞክራሲ ለስምና፣ ብሎም የውጪውን ዓለም ለመሸምገያ እንጂ በእውን ሥራ ላይ እንደማይውል እንገነዘባለን። የወታደሩና የስለላ መዋቅሩ እንደሌሎቹ ሁሉ፣ "ለህገ መንግሥቱ ሳይሆን በህወሃት ለሚመራው ስውር መንግሥት ነው" ተጠሪነታቸው። በአሁኑ ጊዜ፣ በተለይም ከምርጫ 1997 ዓ ም በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰቱትን በጣም አስከፊ ሁኔታዎች የተመለከተ ሁሉ ይህን የመጽሐፉን ጽንሰ ሐሳብ (theory) ከጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ አይመስለኝም። በዚህ ሁኔታ ምርጫ፣ ዴሞክራሲ፣ ወዘተ ብለን የምንመኘው ሁሉ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንደማለት ነው።

ይህ የስውር መንግሥት የረዥም ጊዜ አጀንዳው በሕዝቡ ላይ የስነ ልቦና (ሳይኮሎጂ) ጦርነት ማካሄድ፣ ተቃዋሚውን መከፋፈል፣ በግል ጋዜጦች ላይ መዝመት፣ የስለላ መረቡን በስፋትና በጥልቀት መዘርጋት፣ ከወታደራዊ ዝግጅቱ አኳያ፣ "ጠላትና እኛ" ብሎ ሕዝቡን እንደ ጠላት መፈረጅና ሽብርንም እንደ ትግል ዘዴ መጠቀም ነው። እንደ መጽሐፉ ገለጻ ሁኔታው ይህን ሲመስል፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካን የሚከታተሉና ሌሎችም ከዚህ መጽሐፍ የሚያገኙት ትምህርትና ግንዛቤ አለ ማለት ነው። ደራሲው በመደምደሚያው ምዕራፍ ላይ ምርጫ 1997 ዓ ምን

ይተነትናሉ። ቀጣዩ ሂደት ምን መሆን እንዳለበት አቅጣጫውንም ያመላክታሉ። አማራጭ የሚሆኑ ሃሳቦችንም ይሰነዝራሉ።

በመጨረሻም፣ መጽሐፉ የውጪ ኃያላን ሚናን በተለይም የዩኤስ አሜሪካንና የቻይናን ጣልቃ ገብነትን ከሁለቱ አገሮች ብሔራዊ ጥቅም አኳያ ይዳስሳል። ምንም እንኳን "የአሜሪካም ሆነ የምዕራብ መንግሥታት ጠንካራ መንግሥት መፈጠርን አይፈልጉም" (ገጽ 244) ብሎ መጽሐፉ ቢደመድምም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ሌላ አስተያየት መሰንዘር ይቻላል። በእርግጥ የእነዚህ መንግሥታትን ብሔራዊ ጥቅም የሚጻረር ጠንካራ መንግሥት አይፈልጉም። ሆኖም፣ ጠንካራ መንግሥታት ሆነው የእነዚሁኑ የውጭ ኃያላንን ጥቅም ያሚያስከብሩላቸው እንደ ደቡብ ኮሪያ ያሉትን ይፈልጋሉ።

በተለይ አሸባሪዎችን ለመዋጋት ኢትዮጵያ የአካባቢው አረጋጊ ጠንካራ ኃይል (Regional Hegemonic Stabilizing Force) ተብላ ስለምትገመት፣ በአገሪቷ ውስጥ የሚካሄደው ኢዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለፕ/ት ቡሽ መንግሥት በጣም አሳሳቢ አይደለም። በቅርቡ የእስራኤል የመከላለከያ ኃይል የታሪክ ክፍል ሃላፊ ሻውል ሼ፣ የጻፉት መጽሐፍን፣ "የቀይ ባህር አሸባሪ ትሪአንግል" (The Red Sea Terror Triangle) ማየቱ ይረዳል።

ቻይናን በተመለከተ፣ እርግጥ ለቻይና፣ ዴሞክራሲ፣ ሰብዓዊ መብት፣ ወዘተ፣ ተብለው በምዕራቡ አገር የሚወደሱት ሃሣቦች ደንታ አየሰጣትም። የሚያሳዝነው፣ በ1960ኛዎቹ ውስጥ ቻይና ከአፍሪቃ ሕዝብ ጎን ተሰልፋ ለነፃነት ትግል አጋዥ እንዳልሆነች ሁሉ፣ አሁን ለአፍሪቃ ሕዝብ ጀርባዋን በመስጠት ከጨቋኝ ገዥዎችና ከዘር አጥፊዎች (ሱዳን፣ ዳርፉርን ይመለከታል) ጋር መግጠሟ ያሳዝናል። ይህንን በተመለከተ በዚህ መጽሐፍ ገምጋሚ

የተደረሱትን ሁለት ጽሑፎች ማየት ይረዳል። ["China: Ethnic Politics, Nation Building and Its Global Role", Journal of South Asia and Middle Eastern Studies, Fall 2005, Vol XXIX No.I] እንዲሁም በቅርቡ ታትሞ የሚወጣውን ["Building or Bulldozing: The Use and Abuse of Ethnic Politics, the Case of China and Ethiopia", International Journal of Ethiopian Studies, Fall 2006, Vol. 3, No.1] ይመልከቱ።

ደራሲው፣ ኢትዮጵያ ልጆቿን ይዛ በማዕበል እንደምትናጥ መርከብ አስመስለዋታል። ይህች መርከብ የምትሻው ሁኔታዎችን የሚያረጋጉላትን እንጅ ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ሆነው የሚያባብሱትን አይደለም።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሳይጠቀስ የቀረና በኢትዮጵያ ወቅታዊ ፖለቲካ ላይ እንድምታ ያለው ሁኔታ አለ። ይኸውም፣ በአባ ጳውሎስ የምትመራው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያን ጉዳይ ነው። በአሁኑ ጊዜ ይህች ቤተ ክርስትያን ከገዥው ቡድን ጋር በመወገን፣ ከወታደር ዱላ ሸሽተው በድባቧ ስር መጠለያ የፈለጉትን አሳልፋ የምትሰጥ፣ ህፃናት ሲገደሉ፣ የንጹሃን ደም ሲፈስ ዝም የምትል ስትሆን፣ በታሪክ ፊት ተወቃሽ ትሆናለች። እርግጥ ከሕዝብ ጎን የቆሙ አንዳንድ የሃይማኖት አባቶች አልጠፉም። ነገር ግን ያ በቂ አይደለም። ምንም እንኳን ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት ልዩ ናቸው ተብሎ (በሰም መልክ) ቢነገርም፣ በሥራ ግን (ወርቁ) ይህ ሲሆን አልታየም። ደራሲው ብዙ ተቋማት በህወሃት መዳፍ ስር ናቸው ብለው በሚገባ ተንትነዋል። ቤተ ክህነት ከህወሃት የስውር መንግስት ጋር ያላት ቁርኝት በአዲስ መልክ መታየት ያለበትና ወደፊት ልዩ ጥናት የሚጋብዝ ነው።

አሁን በኢትዮጵያ ያለው አቆርቋዥ ሥርዓት (predatory state) በዚህ ከቀጠለ ህዝባችንና አገራችን ወደ ከፋ ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ለምሣሌ፣ ከሌሎች አገሮች ጋር በመሆን፣ ኢትዮጵያ እአአ በ2015 ዓ ም "የዘመኑ የዕድገት ግቦች" (Millenium Dev't Goals) ተብሎ በሚታወቀው ራዕይ ድህነትን ለማስወገድ፣ ሰብዓዊ ክብርና እኩልነትን ለማስጠበቅ፣ ሰላምን ለማስፈን፣ ዴሞክራሲንና አካባቢን በቀጣይነት ለመንከባከብ ቃል የገባቻውን ለማሟላት ትቸገራለች፡፡ ለዚህም ተጠያቂው የኢትዮጵያ መንግሥትና ባብላጫው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተጠቀሱት ሁኔታዎችና ሂደቶች ነው፡፡

በአጠቃላይ፣ አቶ ክፍሉ ታደሰ እንደቀድሞው የጥናት መጽሐፎቻቸው ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፎችና የፖለቲካ ክርክር (discourse) አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ መጽሐፉ መነበብ ብቻ ሳይሆን መጤን ያለበት ነው፡፡